# ተናግረው የሚያናግሩ ሰዎች

በወርቁ አሰፋ (ዶ/ር) ነሐሴ 09 ቀን 2007 ዓ/ም

<u>መግቢያ፤</u>

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ "ተናግረው የሚያናግሩ ፎቶዎች!"[1] በሚል ርዕሥ፤ እ.አ.አ ጁላይ ፳፯ (27) ቀን 2015 ዓ/ም ተዘጋጅቶ፤ በታሪኩ አባዳማ በቀረበው ጽሑፍ ላይ የተነሱ ጥያቄዎችንና ጉድፎችን ነቅሶ በማውጣት፤ ከጠያቂው መልሥ በመስጠት፣ ከአንባቢያን ሚዛኑን የጠበቀ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተወጠነ ነው።

የታሪኩ አባዳማ ጽሑፍ በ14 አንቀፆች (ፓራግራፍ) ተዋቅሮ በሁለት ገፆች የተመጠነ ነው። ታድያ በቅርጫት ኳስ (በአራዳ አጠራር የቅርጫ ኳስ) ፍቅር የተነደፉ ይመስለኛል፤ በአንድ ወቅት አሜሪካዊው ማይክል ጆርዳን ተናገረው በሚሉት የእንግሊዝኛ ቃል (ያለ ትምህርተ ጥቅስና ምንጭ) ጽሑፋቸውን ጀምረው፤ ይህንኑ ቃል የጽሑፋቸው መደምደሚያ አድርገውታል።

**"ሳያቃጥል በቅጠል"**

ከጽሑፉ መረዳት እንደቻልኩት፤ ባልተጠበቀ ሁኔታ የተፈጠረ ክሥተት ከቁጥጥር ውጪ እንዳይሆን ቶሎ ብለው ለማስናከል የሰነዘሩት የፈሪ ዱላ ይመስላል። በዚህ ዱላም ከመነረት ያሰቡት ሥም የከሸ ግለሰብ (በአቶ ታሪኩ አባዳማ አገላለፅ፤ ጋዜጠኛ ተብዬ) ግምቦት 7 በሻዐቢያ ድጋፍ ያራምዳል ለሚባለው የትጥቅ ትግልና ፕሮፓጋንዳ እንቅፋትና ምቀኛ ናቸው። ሆኖም ፀሐፊው "ተናግረው የሚያናግሩ ፎቶዎች!"ን ለንባብ ሲያቀርቡ፤ ለመፃፍ የተገፋፉበትን ምክንያት አድበስብሰው፤ በአሽሙርና ሽሙጥ ከመግለፅ ባሻገር ያነጣጠሩበትን ሁነኛ ግለሰብና የፅሑፍ ርዕሥ በአደባባይ ለትችት አቅርበው ሰው እንዲነጋገርበት ለማድረግ ድፍረት አላገኙም። እኚህን ግለሰብ ከያዛቸው የፍርሃት ቆፈን ፈልቅቆ ለማውጣት፣ እንዲህ የተጨነቁበትንና ቅስፈት የሆነባቸውን ጉዳይ አብረን ለመዳሰስ፣ ያነሷቸው ጥያቄዎችም ተገቢ ምላሽ አግኝተው እንዲረጋጉ፤ አንባቢያንም ሚዛኑን የጠበቀ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ይህን ፅሑፍ ለማቅረብ ተነሳሳሁ። በየደረጃውም በአንባቢያን አዕምሮ ውስጥ የሚጉላሉ ሃሳቦችና ተያያዥ ጉዳዮች የሚሳከሙበትን አቅጣጫ ምናባችን ሲረዳ የብርታት መኖ ይሆኑታል። ስለዚህ በትዕግሥት እስከ ፅሑፉ ፍፃሜ አብረን እንዝለቅ።

ታሪኩ አባዳማ ከፅሑፋቸው ርዕሥ ግርጌ ያስቀመጡት ትምህርተ ጠቅስና ምንጭ አልባ የማይክል ጆርዳን አባባል፤ በእንግሊዝኛ ተፅፎ ይታያል። ይህም ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መልዕክት ከኢትዮጵያ የአበው ብሂሎችና ከቅኔው በበለጠ ወለል አድርጎ እንደሚገልፅላቸው በማሰብ፤ በቀጥታ የተንደረደሩት በስሙ ያልጠቀሱትንና ጋዜጠኛ በሚል ማዕረግ በድረ ገፆች ላይ ይጽፋል ያሉትን ምናባዊ ግለሰብ ስብዕና ለማጉደፍ ነበር። እስቲ እዚህ ላይ አፈር ልሁንልዎትና ነገር ሲጀመር፤ አንባቢም እንዳይደነግጥ ለስለስ አድርጎ ቀስ በቀስ ወደ ዋናው ጉዳይ ይገባል እንጂ ከጅምሩ ቱግ! ቱግ!! ቱግ!!! ከእንደ እርስዎ ዓይነት የዲሞክራሲ ጠበቃና ለሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነኝ ባይ ያልጠበኩት ትዕይንት ነበር። ቢሆን ግለሰቡ በድረ ገፆች ያሰራጯቸውን ፅሑፎች ርዕሥ ለኛም በገለፁልንና ተረድተነው እንደ እርስዎ ቆሽታችን እርር ድብን ባለ። ሊያም የአስተሳሰብ ልዩነት መሆኑን አመዛዝነን እርስዎን ለማፅናናት በታደልን ነበር።

ታሪኩ አባዳማ ሃሳባቸውን መግለፃቸው ችግር የለበትም። ሃሳብ ደግሞ በተለያየ መንገድ ይገለፃልና። ነገር ግን አካሄድዎ፤ በገሃድ የወጣና የአደባባይ ፀሐይ እየሞቀ ያለውን የሰሞኑን ጉዳይ አድበስብሰው የመረጃ ፍሰቱን አቅጣጫ በማስለወጥ፤ የራስዎንና የመሰሎችዎን ዓላማና ጥቅም ለማስከበር እንዲሁም ጊዜ ለመግዛት የሚድሁ ያስመስልዎታል። ስለዚህ "ተናግረው የሚያናግሩ ፎቶዎች!" በሚል ርዕሥ ካቀረቡት አስተያየትዎ፤ የባላንጣዎን ምላሽ በተስፋ እየተጠባበቁ ስለመሆንዎ መገመት አያዳግትም። አንዳንድ እንደ እርስዎ ያሉ የድረ ገፅ ታዳሚዎችም ሰውየው የተጠመዱበትን ጠቃሚ ሃገራዊ ጉዳይ ትተው እራሳቸውን ለመከላከል የሚሰነዝሩትን የመልሥ ምት ለማየት የሚቋምጡ አይታጡም። እኔም እስከ አሁን መልስ የሚሰጥ ይኖራል ወይም እርስዎ በሁለተኛ ዙር ይዘው የሚቀርቡትን አይቼ እንማማራለን በሚል ተስፋ ስጠብቅ ነበር። በጽሑፍዎ ላይ የተነሱት ጉዳዮች አነጋጋሪና በጥንቃቄ መታየት ያለባቸው ስለሆኑ በዚህ አጋጣሚ ጭንቀትዎን ለማቅለል ልድፈር፤ ታዲያ እርስዎም ይተባበሩኝ። እ.አ.አ ጁላይ 21 ቀን 2015 ዓ/ም "እዎ! የኤርትራው ፎቶ ይናገራል"[2] በሚል ርዕሥ በጋዜጠኛ ደምስ በለጠ በኢትዮሚዲያና በኢትዮፓትሪዎትስ ድረ ገፆች ላይ ለኢትዮጵያውያን የቀረበው በጣም ጠቃሚ መረጃ አዘል ፅሑፍ ዱብዕዳ ሆኖብዎት፤ በዚህ ሰበብ "ተናግረው በሚያናግሩ የፎቶዎች ታሪክ" የተሰማዎትን ስሜት በቁጭት ሊገልፁ እንደወሰኑ፤ የኢትዮጵያን የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ለሚከታተል ማንኛውም ግለሰብ መገመቱ አያዳግትም።

ከሁሉ የሚገርመው ግን፤ ታሪኩ አባዳማ "የተረገጡ ዲሞክራሲያዊ ድሎችና መዘዛቸው" በሚል ርዕሥ በኢትዮሚዲያ ላይ እ.አ.አ ጁላይ 24 ቀን 2015 ዓ/ም በወጣው ፅሑፋቸው አማካይነት እ.አ.አ ጁላይ 21 ቀን 2015 ዓ/ም በዚሁ ድረ ገፅ ላይ ቀድሞ የወጣውንና፤ "እዎ! የኤርትራው ፎቶ ይናገራል" በተሰኘው የጋዜጠኛ ደምስ በለጠ ዘገባ ላይ አንድም ቃል አለመተንፈሳቸው ለምን ይሆን? ከበላይ አካል የሚሰጥ ትዕዛዝ ስላልደረሳቸው? መልዕክቱ እያደር የሚቆጠቁጥ ሆኖ? ወይስ "በተረገጡ ዲሞክራሲያዊ ድሎችና መዘዛቸው" የሚደግፉትን የፖለቲካ ቡድንና ግለሰብ ተክለ ሰውነት እስኪገነቡ ነገሩን በይደር ለማቆየት አስበው?

## “ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኰነነኝ”

ታሪኩ አባዳማ “ተናግረው በሚያናግሩ ፎቶዎች” ታከው ባስነበቡን ትረካቸው ላይ ዶር ብርሃኑ ነጋና አቶ ነአምን ዘለቀ በአሥመራ አቀባበል ሲደረግላቸው የተነሱት ትኩስ ፎቶግራፍ ነው በሚል፤ በድርጅታቸው ግምቦት 7 እና በደጋፊዎቻቸው አማካኝነት በድረ ገፆችና በኢሳት ላይ ሲሰጣጡ የሰነበቱ ምስሎችን አስመልክቶ፤ በገፅ ፩ በሁለተኛው አንቀፅ ላይ እንዲህ ይላሉ። “ከውነቶች ጀርባ የተደበቁ ውሸቶች፣ ከነኚያ ውሸቶች ጀርባ የተደበቁ ውነቶችን እየቀላቀሉ መናዘዝ ከፅድቅ አያበቃም። እንደ ቡትቶ ጨርቅ ያንንም ያንንም ደራርቶ፣...... ጋዜጠኛ በሚል ማዕረግ የግል ጥላቻን በድረ ገፅ ላይ ማሰራጨት አሳፋሪና ቀላልነት ነው።”

ታሪኩ አባዳማ ከላይ ያቀረቡት አስተያየት በመረጃ ያልተደገፈና ከሥነ አመክንዮ ያፈነገጠ ተራ ዒልት ነው። በጋዜጠኛው ተደራረቱ ስለሚሉትና ስላስተካከፊው የግል ጥላቻ ምንነትና በማን ላይ እንዳነጣጠረ፤ ለዚህም እርስዎ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያውቁትን አንድም ነገር አልተነፈሱም። ባላንጣዎን አስፈራርተው አፍ ለማስያዝና ሥሙን በማጥፋት ተዓማኒነትን ለማሳጣት አምጠው የፈጠሩት መላ ሩቅ አያስኬዶትም። እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባዎት አንድ ቁምነገር አለ። በሙያው ሥነ ምግባር የተካነ ጋዜጠኛ ተልዕኮውን አስመልክቶ የሚፅፈው ፅሑፍ፤ ከፅድቅ ሳይሆን ሕዝብን ትክክለኛ መረጃ ለማስጨበጥ ነው። እርስዎ “ተናግረው በሚያናግሩ ፎቶዎችዎ” ላይ ያቀረቡትን ፅሑፍ ዋና ቅጅ ወደ መንግሥተ ሰማያት ልከው፤ በግልባጩ እኛን አሳውቀውን ከሆነ፤ የፅድቁ ሠርተፊኬት ሲደርስዎ አደራ አይርሱን።

ጋዜጠኛ ደምስ በለጠ በዕውነተኛ ሥሙ በድረ ገፆች ላይ ላወጣቸው ፅሑፎቹ ኃላፊነትን ወስዶ ተጠያቂ መሆኑን አሳይቷል። እ.አ.አ ጁላይ 25, ቀን 2015 ዓ/ም በኢትዮጵያ አንበሶች ክበብ የፓልቶክ መወያያ መድረክ ተሳትፎው ይህንኑ አረጋግጧል። (የኛ ሰው በአሥመራ ቃለ መጠይቁን ለማዳመጥ www.ethiopatriots.com www.ethiopatriots.org www.ethiopianreview.com ድረ ገፆችን ይመልከቱ)

http://ethiopatriots.org/Interview/Demis-Belete_Interview-Ethiopian-Lions-Club_P1.mp3

http://ethiopatriots.org/Interview/Demis-Belete_Interview-Ethiopian-Lions-Club_P2.mp3

ታሪኩ አባዳማ እርስዎ ከነ ሞክሼዎ በደቦ/በጅጊ ከሚፅፉበት የብዕር ማማ ላይ ወርደው በዕውነተኛ ሥምዎ የምንተዋወቀው መች ይሆን? ካልሆነም በማስተዋውቁ ልረዳዎት እችላለሁ።

## “ነገርና የወለዱት ልጅ ሲመስል ጥሩ ነው”

እኚሁ ፀሃፊ በገፅ ፩ በሦሥተኛው አንቀፅ ላይ "ጋዜጣ እና ጋዜጠኛው ምን ያገናኛቸዋል - ወሬ እና ወሬ አቀባዩ እንዴት ይዛመዳሉ? ለመሆኑ በምን መሥፈርት ነው አንድ ሰው ጋዜጠኛ በሚል ማዕረግ የሚጠራው፤ . . . . ወያኔ አዲስ አበባ በገባ ማግሥት ያሻችሁን ፃፉ ተብኳል በሚል ከተማይቱን እንደ ሱናሚ ያጥለቀለቀው ጋዜጣ እንደ ጎርፍ አግበስብሶ ወደ ወሬ አቀባይነት ያመጣቸው ሁሉ ጋዜጠኞች ነበሩ? ሙያው የሚጠይቀውን ስነምግባር እና ብቃት ሳይሟሉ እንዲያው ከጎዳና ላይ ተነስቶ ጋዜጠኛ መባልስ ተገቢ ነው?....."

በማለት ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች በእርግጥ መልሱ ጠፍቷቸው አይደለም። ፀሓፊው የተደናገሩ መስለው ለማደናገር፤ ያልገባቸው የዋህ መስለው ሌላውን ግራ በማጋባት በሰው ምናብ ውስጥ ጥርጣሬን በመዝራት መረጃን ሳያላምጡ የሚውጡ የነፈዙ ግለሰቦችን ለማብቀል ሲድሁ ይታያል። ለእንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ሰለባ የሆኑ ግለሰቦችም በቀላሉ በእነ ታሪኩ አባዳማ የፕሮፓጋንዳ ወጥመድ ውስጥ በመውደቅ እንደማይነጥፍ ጥገት እየታለቡ፤ የሻዕቢያን ዕኩይ ዓላማ አስፈፃሚ የሆኑ ግለሰቦችን ደንደሥ ሲያፈረጥሙ ታይቷል። እርስዎና መሰሎችዎም “ተናግረው አናገሩንና” በዚህ መልክ ተቀፍድደው የተያዙ የዋህ ወገኖቻችንን ለማባነን ብዕሬን አነሳሁ። ጋዜጣና ጋዜጠኛ፣ ወሬና ወሬ አቀባይ በሚገባ የሚገናኙበትና የሚዛመዱበት ብሎም የሚያስተሳሥራቸው ፋይዳ አለ። ልክ እንደ ሸማና ሸማኔ፣ በሬና ገበሬ፣ ቤተክርስቲያንና ክርስቲያን፣ ማህበርና ማህበርተኛ ወዘተ ማለት ነው።

የሰው ልጅ ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ጀምሮ እስከ ደረስንበት ፳፩ኛው (21ኛው) ክፍለ ዘመን፤ የዕለት ተዕለት ኑሮውን አሸንፎ በዚህች ዓለም ላይ ተደላድሎ ለመኖር ያመቸው ዘንድ ከወጠናቸው ስኬታማ ትልሞች ዋነኛው ማህበራዊ የሥራ ክፍፍልን ፈጥሮ በየደረጃው ተግባራዊ ማድረጉ ነው። በዚሁ የሥራ ክፍፍል ውስጥ በምሳሌነት ከሚጠቀሱት፤ የወታደራዊ ሳይንሥ ሙያ፣ የሕክምና ዘርፍ ሙያ፣ የትምህርት ዘርፍ ሙያ፣ የምህንድስና ዘርፍ ሙያ፣ የተፈጥሮ ሳይንሥ ዘርፍ ሙያ፣ የማህበራዊ ሳይንሥና የሥነ ጥበብ ዘርፍ ሙያዎች ወዘተ... ጥቂቶቹ ናቸው። በእነዚህም የሙያ መስኮች ከተለያዩ ተቋማት ሰልጥነው፤ የሙያው ሥነምግባርና ግዴታው የሚጠይቀውን በማሟላት ወደ ሥራው ዓለም የሚሰማሩትም፤ በሙያቸው እርከን በየደረጃው በሚያገኙት "ማዕረግ" ይጠራሉ። የጋዜጠኝነት ሙያ፣ ክብርና ማዕረጉም ከዚህ ተለይቶ አይታይም። ታዲያ ታሪኩ አባዳማ ከኢትዮጵያም ሆነ ከውጪው ዓለም በጋዜጠኝነት ሙያ ሰልጥነው የተመረቁ ግለሰቦች ዶሴ የሚገላበጥበት የመረጃ ቋት በመዳፋቸው ተዳብሶ የሚገመገም ይመስል፤ በጽሁፋቸው የማዕረጉ ሰጪና ከልካይ ለመሆን ሲቃጡ ተስተውለዋል። ብዕራቸውንም ካነሱበት ዓላማ፤ በልባቸው ተሰበው "ከጎዳና ላይ ተነስቶ ጋዜጠኛ መባልስ ተገቢ ነው?" በማለት አንባቢያን እንዲፈርጇቸው ተማፅነው ዕውነትን በሃሰት ለመጋረድ ቁም

ሥቅላቸውን ሲያዩ ታዝበናል። ዳሩ ግን ጋዜጠኛ ደምስ በለጠ ሙያው በሚጠይቀው የትምህርት መሥክ ሰልጥነው በብቃት የማስተርስ ድግሪ የተቀበሉና በጋዜጠኝነትም የረጅም ዓመት የሥራ ልምድ እንዳካበቱ ይታወቃል።

በዚህ ባለንበት የመረጃ ዘመን ሰው በማዕረጉ ወይም በሌጣው ፅፎ ሃሳቡን ቢገልፅ፣ ያለውን መረጃ ቢያካፍል፤ ምንስ ችግር አለበት? ሁላችንም የምንታገለው የሰው ልጅ ያለተፅዕኖ ሃሳቡን በነፃነት መግለፅ እንዲችል አይደለምን? ታሪኩ አባዳማ እንዲህ የተጨነቁበትና የተብከነከኑበት ምክንያት ግልፅ ነው። እንደ ጋዜጠኛው ወደ ኤርትራ ተጉዘው በአይንዎ አይተውና አስተውለው፣ በጆሮዎ ሰምተው፣ በእጅዎ ዳሰውና በአዕምሮዎ መዝነው ለሕዝብ የሚያቀርቡት የማስተባበያም ይሁን የመሚገቻ ተመጣጣኝ መረጃ ስለማይኖርዎት ነው።

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ኃላፊነት በጎደለው መልኩ፤ "...ወያኔ አዲስ አበባ በገባ ማግስት ያሻችሁን ፃፉ ተብኳል በሚል ከተማይቱን እንደ ሱናሚ ያጥለቀለቀው ጋዜጣ እንደ ጎርፍ አግበስብሶ ወደ ወሬ አቀባይነት ያመጣቸው ሁሉ ጋዜጠኞች ነበሩ?" በማለት ታሪኩ አባዳማ በጽሑፋቸው ያቀረቡት ስላቅ ነው። እ.አ.አ በ1990ዎቹ መጀመርያ ላይ የቀዝቃዛው ጦርነትን መክሰም ተከትሎ፤ በዓለማችን የነበረው የፖለቲካ ኃይል ሚዛን ሲዛባ፤ የሃገራችን አንድነትና ሕልውና አደጋ ላይ ወድቆ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። በዚያ የታሪክ አጋጣሚም ሲጠበቅ የነበረው፤ የወቅቱን የኢትዮጵያ መንግሥት ጨምሮ ሁሉን የፖለቲካ ተቀናቃኝ ድርጅቶች ያካተተ የሰላም ድርድርና ብሔራዊ ዕርቅ ሊሳካ አልቻለም። በተለይ በለንደኑ ጉባዔ በአሜሪካና በእንግሊዝ መንግሥታት ተፅዕኖና ይሁንታ፤ ወያኔ፣ ሻዐቢያና ኦነግ የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የወደፊት ዕድል እንዲወስኑ ሲደረግ፤ መዘዙም ሃገራችን እንደ ሱማሊያና ሩዋንዳ በእርስ በርስ ጦርነት ተናውጣ፤ እንደ ዩጎዝላቪያ ልትበታተን እንደምትችል ሲተነበይና ሲሟረትብን እንደነበር ዛሬ እንደ ታሪክ እናስታውሰዋለን። ሆኖም ከአያሌ ዘመናት ዕምነቱን፣ ባህሉንና ነፃነቱን ጠብቆ፤ ተቻችሎ በአንድነት የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ባለፉት ዓመታት ያጠካበትን የጥፋት አደጋና ሟርት አምክኖ አንድነቱን ለመጠበቅ፤ ከፍተኛ የንብረት፣ የአካልና የሕይወት መሥዋዕትነትን ከፍሏል፤ በመክፈል ላይም ይገኛል።

የታሪኩ አባዳማ "የሱናሚ ጎርፍ ግብስብስ" ሥላቅም እ.አ.አ በ1990ዎቹ መጀመርያ ላይ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ያነጣጠረውን የጥፋት ተልዕኮ ለመመከት በግምባር ቀደምትነት የተሰለፉ ምሁራን፣ ጋዜጠኞችና አገር ወዳድ ዜጎች በመሰረቱት የነፃው ፕረስ ላይ ማነጣጠሩ፤ "አህያውን ፈርቶ ዳውላውን" ነውና ትኩረትዎን በዛው "ተናግረው የሚያናግሩ ፎቶዎች!" ላይ ቀሽትዎን ካሳረረዎት ጋዜጠኛ ጋር ቢያደርጉት መልካም ነበር። ስለ ጋዜጠኝነት የሙያ ሥነምግባርና ክህሎት ተናግረው ሲያናግሩን፤ የአደባባይ ፀሐይ የሞቀውንና በሙያና በችሎታ ሳይሆን፤ በዘመድ አዝማድ፣ በአምቻ ጋብቻና በታማኝነት ተጠርናፊ ስለሆነው "ኢሳት" እንዲሁም ሻዐቢያ በሚቆጣጠረው የኤርትራ ምድር ውስጥ ስላለው የሰብዓዊና ማህበራዊ ቀውስ እስከ ዛሬ ምንም አለመተንፈስዎ ነፃው ፕረስን ለማሸሚጠጥ ያልዎትን የሞራል የበላይነት እጅግ ያኮሰምናል። ነፃው ፕረስና አባላቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን ጠብቆ ከሕልውናው ጠንክሮ እንዲታገል ብሎም በሃገራችን የሕግ የበላይነትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን የደረጉት ከፍተኛ አስተዋፅዖ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በወርቅ ቀለም ተጽፎ ይገኛል።

ወረድ ብለው በአራተኛው አንቀፅ ላይ "ውነትም አዲስ ዘመን ላይ ነን!!" ይላሉ ፀሐፊው በማጋነን የተደነቁ መስለው። መልሱም፤ አዎ! 21ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ዘልቀናል። የሰው ልጅ አንድን ጉዳይ በሚመለከት እጅግ የበዙ መረጃዎችን ያገኛል። ከዚያም አጣርቶና መዝኖ ትክክለኛውን ቁምነገር ላይ ማዋል የሚችልበት ዘመን ላይ ነን።

በስድስተኛው አንቀፅ ላይ ደግሞ የግምቦት 7 መሪን የአሥመራ ጉዞ አስመልክቶ የተናፈሱ ወሬዎች ላይ ነፍስ ለመዝራት "እኔን በሚመለከት የግንቦት 7 መሪ ትግሉ አካባቢ መኻዛቸው ለምን እንደ ዜና እንደቀረበ (ያውም ሰበር ዜና) አልገባኝም።" ይላሉ፤ ይህን እንቅልፍ የሚነሳ ሰበር ዜና በሚመለከት አንባቢና ጋዜጠኛውን ከመጎትጎት አቅራቢውን "ኢሳት" ማነጋገሩ ይቀልዎት ነበር።

## "ካም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ"

ታሪኩ አባዳማ ከላይ ነፍስ ሊዘሩለት የዳዱትን የግምቦት 7 መሪ የአሥመራ ጉዞ ታሪክ፤ በሰባተኛው አንቀፅ ላይ ተክለ ሰውነት ገንብተው ወደ ሳዋ ለማምጠቅ ሲጣደፉ ታዝበናል። የነፃነት ታጋዮችን በሃገራችን አሰልጥነን፤ በሽምቅ ውግያ የትግል ሥልት፣ አመራርና ጥበብ ክነን ለውጤት እንዳበቃን፤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኩራት የሚናገረው ነው። ነገር ግን ለነፃነት ትግል ማጣቀሻ፤ ከኢትዮጵያ አብራክ የወጡ አርዓያ አርበኞችና ታጋዮች የሌሉ ይመስል፤ ታሪኩ አባዳማ ለግምቦት 7 መሪ ገድል ንግርት ይመጥናሉ ብለው የሚገምቱትን የዓለማችን ዕውቅ ታጋዮችን ፍለጋ ቁም ሥቅላቸውን እንዳዩ እራሱ ጽሑፋቸው ለአንባቢያን ያሳብቅባቸዋል።

"የትጥቅ ትግል ለመምራት የተሰለፉ ጀግኖች እርምጃቸውን ለማቀካጠፍ ሲሉ በመረጡት ጊዜ እና ቦታ መገኘት አዲስ ነገር አይመስለኝም። እነ ኦሊቨር ታምቦ፣ እምቤኪ የዛሬው ሙጋቤ ወይንም ሚቼ ሳሞራ ማሼል የትጥቅ ትግላቸውን የመሩት በመላው አለም ነፃነት ወዳድ ህዝብ መካከል በመመላለስ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፉ የነበረው ትጥቅ ትግሉን የሚያግዝ ዲፕሎማሲያዊ እና ማቴርያል ድጋፍ ፍለጋ በውጭው አለም መሆኑን ማስታወሱ ይጠቅማል። የፍልስጤም ነፃነት መሪ ያሲር አራፋት ፓለስታይን ምድር የገቡት ጥንካሬ ባስገኘው ከብዙ ዘመን ቁራጥ ትግል እና ድርድር በሁዋላ እንደ ነበረም ማስታወሱ መልካም ነው። እናም የግንቦት 7 መሪ ትግሉን ለማቀካጠፍ ሲል በመረጠው ጊዜና ቦታ ቢገኝ አማራጩ የድርጅቱ አመራር ብቻ ይሆናል።"

አንባቢያን እንደምታስተውሉት ከላይ በዝርዝር ከተጠቀሱት ጀግኖች መሃል የኖቤል ተሸላሚው "የኔልሰን ማንዴላ" ሥም እንደው በዋዛ አልተገደፈም። ግምቦት 7 በቀደመ ፕሮፓጋንዳው አንዳርጋቸው ፅጌን "በማንዴላነት" ሰይሞታል። ስለዚህ "የቂሟርን ለቂሟር"

እንደተባለው ለዶ/ር ብርሃኑ ደግሞ፤ "የታምቦ፣ የእምቢኪ፣ የሙጋቤ፣ የሳሞራና የአራፋት" ክብር፣ ገድልና ጀግንነቱ ተጠቃሎ ተበርክቶላቸዋል። ቼኩቬራና ሆችሚኖቹም ጊዜና ወቅቱን ጠብቀው ብቅ ማለታቸው ስለማይቀር በተስፋ አብረን እንጠብቅ።

እዚህ ላይ ታሪኩ አባዳማ የቀድሞ የነፃነት ታጋዮችን ሥም ጠቅሰው ለግምቦት 7 መሪ የሌለ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ሊያጎናጽፏቸው ይፈልጋሉ። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በራሳቸው ቃል እንደተናገሩት፤ አሁን ከሄዱበት ከአሥመራ የሻዕቢያ መስተዳድር በዓመት ከሚቆርጥላቸው $ 1000000 (የአንድ ሚሊዎን ዶላር) ድርጎ በስተቀር እስከ አሁን ድረስ አንድ መንግሥት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ይፋ የዲፕሎማሲም ሆነ የማቴርያል ዕርዳታ ለግምቦት 7 አደረገ ሲባል ተሰምቶ አይታወቅም። ሆኖም ግን ዶ/ር ብርሃኑ ቀደም ብሎ በቅንጅት ሥም ከዚያም እንደ ግምቦት 7 መሪ ኢትዮጵያውያን በብዛት በሚኖሩባቸው አንዳንድ የሰሜን አሜሪካና የአውሮጳ ከተሞች ተዘዋውረዋል። ይህም ለነፃነት ታጋዮቹ እንደተደረገው፤ ፕረቶኮሉን በጠበቀ የመንግሥታት ጥሪ፣ አጀብና ክትትል ሳይሆን፤ ጥቂት የግምቦት 7 ደጋፊዎች፤ በስብሰባና ኮንፍረንስ ሥም ባዘጋጇቸው መድረኮች ላይ የተወሰነ ነበር። እነዚህን አጋጣሚዎች ተጠቅሞ ወያኔን በመራገም፤ በማሳረግያው የሚረገጠው ጭቤና ዳንኪራ በታሪኩ አባዳማ መለኪያ የግምቦት 7 መሪን ከነ ኦሊቨር ታምቦ፣ ሳሞራ ማሼል፣ ሮበርት ሙጋቤ፣ ታቦ እምቤኪና ያሲር አረፋት ጋር የሚያስተካክላቸው ከሆነ፤ "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" ከመሆኑ ባሻገር፤ የሚነገሩትና የሚፃፉት በኢትዮጵያውያን ሣይላመጥ የሚሠለቀጥ መስኳቸው ይሆናል።

ነገርን ነገር ያነሳዋልና ታሪኩ አባዳማ ከላይ ለፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ መናጀነት በሥም የጠቀሷቸው የአፍሪካ ነፃነት ታጋዮች ያካሄዱትን ቆራጥ ትግል በመከርከም በግምቦት 7 መሪ ወርድና ቁመት ልክ ሲያመጡ፤ የነፃነት ታጋዮቹ አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፉ የነበረው በመካው ዓለም ጎዝብ መካከል በመመካለስ፣ ዲፕሎማሲያዊ እና ማቴርያል ድጋፍ ፍለጋ  አብዛኛውን ጊዜያቸውን በውጭው ዓለም አባክነው እንደነበር ሲገልፁ፤ ከኢትዮጵያ የይሉኝታ ባህልና ግብረገብ ባፈነገጠ ድፍረት ታጅለው መሆኑ ግልጽ ነው።

የነፃነት ትግሉን ዘመን፣ ከያኔው የዓለም ተጨባጭ ሁኔታና የኃይል ሚዛን ጋር ወደ ኋላ ዞር ብለን ስንቃኝ፤ ታጋዮቹ በትግል ዘመናቸው ያሳለፉት ሕይወት ከግምቦት ሰባቱ የዶ/ር ብርሃኑ ደልቃቃ የሃገር ውስጥና የውጪ ኑሮ ጋር በፍፁም ከንፅፅር የሚቀርብ አይደለም። በዓለም ላይ እንዳሻቸው ለመዘዋወር ይቅርና በተወለዱበት ሃገር በነፃነት የመንቀሳቀስ መብታቸው የተገደበና እንደ ወንጀለኛ ሲፈለጉ እንደነበር ሕያው ታሪካቸው ምስክር ነው። አፍሪካውያኑ የነፃነት ታጋዮች በኢትዮጵያና በወቅቱ ከቅኝ ግዛት ነፃ በሆኑ የአፍሪካ ሃገራት የዲፕሎማሲ ድጋፍና ከለላ ሲንቀሳቀሱና ሲረዱ እንደነበር ይፋ የወጣውን "የኔልሰን ማንዴላን" ታሪክ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። የነፃነት ታጋዮቹ ለውጪትም የበቁት እራሳቸውን ለማዝናፍ የፈጠራ ታሪክ ፍለጋ በመኳተን ወይም ደልቷቸው በአውሮጳና ሰሜን አሜሪካ በስብሰባና ኮንፍረንስ ሥም ድል ያለ ድግስ እየደገሱ ጭቤ በመርገጥ ሳይሆን፤ ለምንና ከማን ጋር እንደሚታገሉ፣  ከነማን ጋር ማበር፣ መወዳጀትና መዋል  እንዳለባቸው ጠንቅቀው በመገንዘብ፣ ብሎም በእርስ በርስ መከባበር፣ በመደማመጥ፣ በፍጹም ሃገራዊ ፍቅር ተከነውና ስብዓዊ መንፈስ ተጎናፅፈው፤ በሕዝባቸው መሃልና በቅኝ ገዢዎች በተያዘው ምድራቸው ውስጥ እየተንቀሳቀሱ፤ ለመሰረቱት ዓላማና ግብ ፀንተው በመታገላቸው ነበር።

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ሊያቀራርቧቸው ካሰቡት ነፃ አውጪ ታጋዮች እጅግ በጣም የሚያራርቃቸው አንድ ወሳኝ ቁምነገር ቢኖር በዓላማቸው ፀንተው በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ለመርጋት የሚያስችል ባህርይና የመንፈስ ፅናት  ማጣታቸው ነው። የካቲቱ 1966 ዓ/ም የኢትዮጵያን አብዮት ፍንዳታ ተከትሎ ባደረጉት የፖለቲካ ተሳትፎ በኢሕአፓ አባልነታቸው በከተማ ውስጥ በተካሄደው ትግል ተሳትፈዋል። ድርጅታቸውም ባካሄደው ስልታዊ ማፈግፈግ በ1969 ዓ/ም አሲምባ ገብተው በወሳኙ የትጥቅ ትግል ሳይሳተፉ "በአንጃነት" [3] ተወንጅሉ። ጉዳዩም ተጣርቶ ከድርጅቱ በፈቃዳቸው የተሰናበቱት ኤርትራ ውስጥ ጀበሃ የሚቆጣጠረውን ምድር ከረገጡ በሕዋላ ሲሆን "ከጀበሃ ጋር ለሰባት ወራት" [3] ያህል ቆይተው በሱዳን በኩል በ1972 ዓ/ም አሜሪካ ገቡ። በአሜሪካም ጊዜያቸውን በትምህርትና በሥራ ላይ ያሳለፉና ትዳርም የመሰረቱ ሲሆን በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥትን ለሚቃወሙ ገንጣይና አስገንጣይ ድርጅቶች መሠሪ ዓላማ ለማስፈፀም በተቋቋመው የ "ሆርን ኦፍ አፍሪካ" ውይይት መድረክ ከአዘጋጆቹ አንዱ የነበሩና በዚህም ለአምስት አመታት ያህል ተሳትፈዋል። እ.አ.አ በግንቦት 1991 ዓ/ም በሃገራችን የተፈጠረውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ በወያኔ/ኢህአዲግ ሥርዓት ላይ ባላቸው በጎ አመለካከት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በማስተማር፣ በምክር አገልግሎት ሥራዎችና በኢንቨትመንት መስክ ተሳትፈዋል።



በፎቶግራፉም ላይ እንደሚታየው የዶ/ር ብርሃኑ ነጋና የወቅቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ፈገግታ የነበራቸውን ቀረቤታ ያሳያል። በዚያው አንፃር በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሥርዓቱ የሚደርስባቸውን ተፅዕኖ ለቋቋሙና በ1997 ዓ/ም (እ.አ.አ 2005 ዓ/ም) በተካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ ተሳትፈው ዲሞክራሲና የህግ የበላይነት የሚሰፍንበትን ሥርዓት ለመመስረት ባደርጉት ዝግጅት፤ በውጭና አገር ውስጥ ባለ ሕዝብ ግፊትና ጫና በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ሕብረት ፈጥረው እንደነበር ይታወሳል። በተፈጠረው ሕብረት ውስጥ በነበሩ ድርጅቶች መሃከል በተነሳው መጠነኛ አለመግባባት፤ አንጋፋው የመካው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና ኢደፓ ከሕብረቱ እራሳቸውን አግልለው ሌላ አቀናጅቶ ለውጤት የሚያበቃ የጋራ ድርጅትን መሠረት ሲጥሉ፤ ከሕብረቱ ጋር በጋራ ጉዳዮች ላይ ለማበር ቀና ነበሩ። በዚያው ትይዩ

ከሻዐቢያ ጋር የባድሜን ጦርነት ተከትሎ ሕወአት ውስጥ በተፈጠረው መከፋፈል፤ ከወያኔ/ኢህአዲግ ቀረቤታ ያላቸው ምሁራን በታማኝ ተቃዋሚነት ፓርቲ መሥርተው ሕዝባዊውን ትግል እንዲቀላቀሉ ተደርጓል። ዶ/ር ብርሃኑና ፕሮፌሰር መስፍን የመሠረቱት "ቀስተ ደመና" እና የፕሮፌሰር አለማየሁ ረዳ "ኢዲኢ" መኢአድና ኢደፓን በመጠጋት "የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ" አባል ሆኑ። (በዚህ የታሪክ አጋጣሚ ዙርያ ስለተፈጠሩ ክስተቶች ብዙ የተባሉና የተፃፉ ጉዳዮች ስላሉ እንደ አስፈላጊነቱ በሌላ ርዕሥ የምመለስበት ይሆናል።)

ዶ/ር ብርሃኑ ቅንጅት ውስጥ አንጃ እንዲፈጠርና ድርጅቱ እንዲከፈል በግምባር ቀደምትነት የተሰለፉ ሰው ነበሩ። ይህም ድርጅት ወደ "መኢአድ"ና "አንድነት" ሲከፈል ከአንድነት ጋር ጥቂት ተጉዘው ባለመስማማታቸው፤ እራሳቸው የሚመሩት ግምቦት 7 የተባለ ድርጅት መሰረቱ። ከዚያም ግምቦት 7 ኦነግን ጨምሮ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር "ጥምረት" ፈጠረ ተባለ። ያም ለጥቂት ወራት ከተናፈሰ በህዋላ፤ ግምቦት 7 ስለሚያንቀሳቅሰው ጦር በሰፊው ተወርቶ ሳንጠግበዉ፤ ዝናር ታጥቀው አዳፍኔ በትከሻቸው ተሸክመው በፕሮፓጋንዳው ፎቶ ላይ የታዩት ሁለቱ "የግምቦት 7 ተዋጊ ሃይል" አባላት፤ ከድርጅቱ ባፈነገጠው "ግንቦት 7 ዲሞክራቲክ" በተሰኘው ቡድን ራዲዮና ድረ ገፅ ላይ የድርጅቱን ከዕውነት የራቀ ፕሮፓጋንዳ ከማጋለጣቸው በላይ ኤርትራ ውስጥ በትግል ሥም እየተመለመሉ በተወሰዱ ኢትዮጵያውያን ላይ የተደረገውንና በመደረግ ላይ የነበረውን ኢሰብዓዊ ድርጊት ገሃድ አውጥተውታል። ይህና ሌሎች ከሻዐቢያ በተለያየ ወቅት አምልጠው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን የሰጡት ቃለመጠይቅ ከዋሺንግተን ዲሲ በሚተላለፈው የአቶ ምርጫው ስንሻው "የኢትዮጵያዊነት ራዲዮ"፣ በአቶ ጌታቸው ረዳ "ኢትዮጵያን ሰማይ ብሎግ" ላይ ለሕዝብ የቀረቡ ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች አቶ ያሬድ ኃይለማርያም ይህን አስመልክቶ ሰፊ ዘገባ ማቅረቡ ይታውሳል። ዶ/ር ብርሃኑ ከግምቦት 7 መሪነት ወደ ጥምረት ከዚያም ግምቦት 7 ከስሞ፤ የግምቦት 7 አርበኞች መሪ በመሆን ወደ አሥመራ አቅንተዋል። ታዲያ ታሪኩ አባዳማ የማይመሳሰለውን ለማመሳሰል እንዲህ በከንቱ ደክመው፣ ሌሎች አጋሮቻቸውን በተመሳሳይ ቅኝት እንዲጽፉ መገፋፋቱ ከትዝብት አልፎ በኃላፊነት ያስጠይቃል።

ጋዜጠኛ ደምስ በለጠ የግምቦት ሰባት አመራርን ወደ አሥመራ መውረድ በሚመለከት የሚቀርቡ ዜናዎች ከፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ውጪ ወጥነትና ግልፅነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ማሳሰቡ አግባብ ያለውና ብዙዎች ይስማሙበታል። የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ከሻዐቢያ ጋር በሚደረግ ቁርኝት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሚመጣ በጎ ነገር መኖር አለመኖሩን በመረጃ በተደገፈ ተጨባጭ ጉዳይ ላይ ተወያይቶና ተነጋግሮ መፍትሄ በመፈለግ ነገሩን መቋጨት ሲገባ፤ ከዚህ ለመሸሽ የተመረጠው አማራጭ ግለሰብ እንደ ጣዖት የሚመለክበትን የሌለ ታሪክ ፈጥሮ ማህበረሰቡን ግራጋባት ነው።

የፒ. ኤል. ኦ (የፍልስጤሙ ነፃነት) መሪ ያሲር አራፋት በአረብ ሊግ የዲፕሎማሲ ድጋፍና ከለላ ሲንቀሳቀሱ እንደነበርና ኢትዮጵያም በአዲስ አበባ "ፒ. ኤል. ኦ" ጽ/ቤት እንዲኖረው ፈቅዳ፤ የዲፕሎማሲ ከለላና ጥበቃ ማድረጓ ይታወቃል። በዚያን ወቅት "ፒ. ኤል. ኦ" እንደ ትግል ሥልት ሲጠቀም የነበረው፤ አውሮፕላን ጠለፋና የሽብር ድርጊቶቹ፤ በአሸባሪ ድርጅትነት ስላስፈረጁት፤ የመሪውም ያሲር አራፋት እንቅስቃሴ እጅግ ጥንቃቄ የተሞላበትና የተገደበ ነበር። በኋላም በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተፅዕኖና ያላሰለሰ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት፤ በኖርዌ በተካሄደው የዕርቅና የሰላም ጉባዔ በእሥራኤል መንግሥትና በፍልስጤም ነፃ አውጪ ግምባር መካከል ስምምነት ተፈጥሮ እንደነበር ይታወሳል። አራፋትም ወገናቸው በብዛት ወደሚኖሩበት የምዕራባዊው የዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻና የጋዛ ሰርጥ ተመልሰው በሰላማዊ ትግል ነፃ የፍልስጤም ግዛትን መስርተዋል። ከዚያም የኖቤል የሰላም ሽልማት አግኝተው ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ዕለት ድረስ የፖለቲካ ፓርቲ እንደ ሽሚዝ ሳይቀያይሩ የመሰረቱት "ፒ. ኤል. ኦ" በውስጡ የሚፈጠሩትን ልዩነቶች አቻችሎ፤ አንግቦ የተነሳውን የፍልስጤም ሕዝብን ጥቅም የማስከበር ተልዕኮ ከግቡ እንዲያደርስ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል።

አፍሪካውያን የነፃነት ታጋዮች ከጅምሩ፤ የሃገራቸው በቅኝ ገዥዎች መያዝን ተከትሎ በራሳቸውና በወገኖቻቸው ላይ ከሚደርሰው ስቃይ፣ በደልና ውርደት ለመገላገል ቆርጠው ሲነሱ፤ በመሰረቷቸው የፖለቲካ ድርጅቶች አማካይነት ነበር። ሆኖም የተነሱበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በድርጅቶቻቸው ውስጥ የሚፈጠሩ ልዩነቶችን በማቻቻልና በመግባባት፣ ትግሉ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ ለድል በቅተዋል። ለዚህም በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሤ ዘመንና በዘመነ አብዮት (ደርግ) የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የሰጠው ሰፊ የዲፕሎማሲ፣ የስልጠና፣ የሞራልና የማቴርያል ድጋፍ ልዩ አስተዋፅዖ እንዳበረከተ በሰፊው ተዘግቧል።

ታሪኩ አባዳማ የግምቦት 7 መሪ ወደ አሥመራ አደረጉት የተባለውን እንቅስቃሴና ስብዕናቸውን ለማጉላት፤ በዓለማችን እጅግ ታዋቂ ከሆኑ ነፃ አውጪ ታጋዮችና የሃገር መሪዎች ታሪክ ጋር እያነፃፀሩ ባቀረቡት ድርሰታቸው ተንጠላጥለው "ተናግረው የሚያናግሩ ፎቶዎችን!" ወግ፤ ጣዕም ለመስጠት በገጽ አንድና ሁለት፤ በስምንተኛው አንቀፅ ላይ እንዲህ ሲሉ ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል። ". . . የጀመርኩት ረቂቅ ወደ ሌላ ይዞኝ ጭልጥ አለ - አዎ ፎቶዎቹ ይናገራሉ - ያናግራሉም፣ ያስቀባጥራሉ። ልጅ ሆኜ አንድ ቄስ ነበሩ። አጋንንት በማስለቀቅ ዝነኛ ናቸው። ፎቶዋቸው አንዳንድ ብር ይሸጥ ነበር። አጋንንት ሰፍሮበታል የተባለ ሰው የቄሱን ፎቶ ሲያይ መቀባጠር መለፍለፍ ይጀምራል። ታዲያ አሁን የትጥቅ ትግሉን ጀማምሬው ነበር የሚለውን ወሬ አቀባይ ሰሞኑን ያየነውን የተቀላቀሉ ወሬ ፎቶ ላይ የምታዩት አገሌ ነው . . . ጥግ የቆመው፣ መሀል የተገተረው . . . እያለ የቋጠረውን ሁሉ ዘረገፈው።"

አዎ! ታሪኩ አባዳማ ከጀመሩት ረቂቅ ወደ ሌላ ይዞዎት የጋለበው ዳማው የሃሳብ ፈረስዎ ወደ ፎቶዎቹ ጉዳይ ባይመልስዎት ኖሮ ካልታሰቡ ሃሳቦች ጋር ተላትመው ሌላ መዘዝ ሊመጣ ይችል ነበር። የሚገርመው የልጅነት ትዝታዎና "ተናግረው የሚያናግሩ የኤርትራው ፎቶዎች" ጉዳይ መገጣጠሙ!

መቼም "ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው" አይበሉኝና፤ በዘመነ አብዮት የወሊሶው ባህታዊ አባ ወልደተንሳይ ከፈጣሪ አምላክ ባገኙት ፀጋ፣ በመስቀልና በጠበል አጋንንትን ሲያስለቅቁና ሕመምተኞችን ሲፈውሱ ነበር። ብዙ ሕዝብም ይህ የጌታ ፀጋ ያመጣውን ድህነትና በረከት ለመቀበል ከተለያየ የሃገራችን አካባቢ ወደ ወሊሶ ደርሶ የተመለሰ፤ ስላየውና ስለሰማው ተዓምራት መሥክሯል።




ጋዜጤኛ ደምስ በለጠ "አዎ! የኤርትራው ፎቶ ይናገራል" በሚል ርዕሥ ባቀረበው መረጃ አዘል ጽሑፍ ላይ፤ ለግምቦት ሰባቱ ዶ/ር ብርሃኑና ለአቶ ነአምን በአሥመራ አቀባበል ሲደረግላቸው የሚያሳይ ፎቶ ተብሎ በራሱ በግምቦት ሰባትና በደጋፊዎቹ ኢንተርኔት ላይ የተሰራጨውን ምስል አስመልክቶ ማብራርያ መስጠቱ ይታወቃል። ጋዜጠኛውም በቀረቡት ሁለት የተለያዩ ፎቶግራፎች ላይ የሲቪል ልብስ ለብሰው የሚታዩትን እንደሚያውቃቸው ሥማቸውን በመጥቀስ ማንነታቸውን ለኢትዮጵያውያን አሳውቋል። በዚሁ ፎቶ ላይ ሦሥት ዓይነት ወታደራዊ የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) ለብሰው ተርታውን የቆሙትን ደግሞ፤ የመጡበትን ወታደራዊ ክፍል (ቅጠልያ ኮፊያ፣ አመድማ ዥንጉርጉር ልብስ (የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ የያዘው) የሻዐቢያ ፣ ቅጠልያ ሬንጀር የአርበኞች ግምባር መለያ መሆኑንና ድምህት በካኪ ዩኒፎርም እንደሚለይ) ጠቅሷል። ይህንንም አስመልክቶ የፎቶው ጉዳይ የሚመለከታቸው ግለሰቦችም ሆኑ ግምቦት 7 ያወጡት የዕርምት ወይም የማስተባበያ ደብዳቤ የለም።




እዚህ ላይ ታሪኩ አባዳማ ኤርትራ ሄደው፣ ኖረው፣ ያዩትና የታዘቡት ወይም የሚያውቋቸው ግለሰቦችና የጦር አበጋዞች ሹክ ያሏቸውን አጣቅሰው፤ መልስ ይሆናል የሚሉት መከራከርያ ነጥብ እንደሌላቸው ያውቁታል። እንደው በሌጣው "ተበላን" (ተፈጄና) በሚል ብሽቀት ነው "የፈሪ ዱላቸውን" ይዘው የተንቆራጠጡት። ጋዜጠኛው ባቀረቡት ቁምነገር ላይ ያላቸውን ተቃዉሞ፣ ትችት፣ ወይም ስህተት ነው የሚሉትን መረጃ በማጣቀስ፣ በወጉ ማረም አሊያም ማስተባበል ሲገባቸው፤ ከርዕሡ ጋር በማይዛመዱ እንቶ ፈንቶዎች ውስጥ ገብተው ሲንደፋደፉ ትዝብት ላይ ወድቀዋል።

በጽሑፋቸው መገባደጃ፤ በገጽ ሁለት፣ አሥራ ሁለተኛው አንቀፅ ላይ "የቁሱ ነገር - ታዲያ እኛ የማውቃቸው ቄስ፣ አጋንንት የሰፈረበት ሰው ፎቶአቸውን ብቻ አይቶ ሲወራጭ ከታየና ዘመድ አዝማድ ካለው እሳቸው ዘንድ ያመጣዋል። እሳቸውም ጠበል ረጭተው መስቀል አሳልመው "...ልቀቅ፣ ለቀህ ወደ መቀመቁ ውረድ..." እያሉ በግዝት አጋንንቱን አዋክበው ከልክፍት ይገላግሉታል..." በማለት ከኤርትራው ጉዞ የፎቶ ታሪክ ጋር የተገጣጠመ የልጅነት የፎቶ ትዝታቸውን ያስኮመኩሙናል። በፎቶው ላይ ያሉት ዶ/ር ብርሃኑ፣ አቶ ነአምን፣ አቶ ኑርጀባ፣ የሻቢያ ወታደሮች፣ የአርበኞች ግምባርና፣ የድምህት ጦር አባላት በአንድ ላይ ሁነው ሲታዩ ፤ ልክ ታሪኩ አባዳማ በልጅነታቸው የሚያውቁት ቄስ ፎቶ ላይ የሰፈረው መለኮታዊ ኃይል፤ አጋንንት ያለበትን ሰው በምድር ላይ እንደሚያስገዝፍ ሁሉ፤ ጋዜጠኛ ደምስን ጨምሮ የግምቦት ሰባትንና የሻዐቢያን ቁርኝት በጥርጣሬ የሚያዩና የሚቃወሙ ሁሉ በኮምፒውተራቸው ገጽ ላይ ተዐምረኛውን ፎቶ ሲያዩ እንዴት እንደለፈለፉና እንደቀባጠሩ እስቲ ገምቱት። ታሪኩ አባዳማ ይህን በዕውን ቀርቶ በሕልማቸው የማያዩትን ተዓምር አደባባይ ላይ ይዘው ሲወጡ፤ እራሳቸውን "የጨሱ አራዳ" አድርገው ገምተው ይሆናል። ዳሩ ግን ያለነው 21ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ነው። የሰው ልጅ አስተሳሰብም ከዕድሜ፣ ከጊዜና ከሥልጣኔ ጋር ዳብሮ ይገራል። እርስዎም ከዋሉት ጋር ውለው፤ በዚያው መለኪያና ቋንቋዎ፤ የሃገርና የሕዝብን ሕልውና የሚመለከት ፋይዳ ሲቀርብ ለማሰናከል ያደርጉትን ጥረት፤ "ወደ ሌላ ይዞዎት ጭልጥ ካለው ጉዳይ ሲባንኑ" እንደሚያዝኑበት በሂደት ይረዱታል።

ታሪኩ አባዳማ በአንቀፅ አሥራ ሦሥትና አሥራ አራት ላይ አሜሪካዊው ማይክል ጆርዳን በአንድ ወቅት ተናገረው የሚሉትን የእንግሊዝኛ ቃል (ያለ ትምህርተ ጥቅስና ምንጭ) አስፍረው፣ " የትርጉሙ ችሎታዬ አቅም ያንሰዋል" በማለት የውርስ ትርጉሙ ከራስጌው ላይ መስፈሩን በመጠቀም ምኞታቸውን ይገልፃሉ። ከዚያም ማሳረጊያውን "ልቀቅ...ወደ መቀመቁ.. ወደ ወያኔ ሰፈር ውረድ!!" በሚል ቃል ጽሑፋቸውን ይደመድማሉ። አጋንንቱ ከሰፈረበት ግለሰብ ላይ ለቆ ወደ ወያኔ ሰፈር ይውረድ ማለታቸው ነው። ክህነቱና ተሰጥዖው ቢኖራቸው ኖሮ አጋንንቱን ወደ ገሃነም ከመላክ ወያኔ ወዳለበት ሃገር ማለትም ወደ ኢትዮጵያ ሊሰዱት ነው። ታዲያ ወያኔው ላይ አጋንንት ታክሎበት!!! ምኑን ተኖረ? እዚህ ላይ ነው የእርስዎ ብልጠት፣ ብልሃት፣ ከሃገርና ከሕዝብ ተቆርቋሪነት አግጥጦ ወጥቶ የከሸፈው።

ማጠቃለያ፤

ታሪኩ አባዳማ በጽሑፋቸው ላይ ያንፀባረቁት ነባራዊውን ዕውነታ ሳይሆን ምኞታቸውን ነው። ለዚሁ ምኞታቸው ስኬት የሚሉት ምናባዊ ገፀባህርይና ግውዙ ተዋናይ በምግባር እንደማይጣጣሙ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በአንክሮ ለሚከታተል የተሰወረ አይደለም። ሆኖም ፀሓፊው ጉዳዩን ሳይገነዘቡት ቀርተው ሳይሆን፤ ሆን ብለው በ "ተጨፈኑ ላሞኛችሁ" ፈሊጥ የታሪክ መረጃዎችን እያዛቡ የጽሑፋቸውን አንባቢ ሁሉ በራሳቸው ቅኝት ለማሾር ነበር።

ስለዚህ፤

1. ታሪኩ አባዳማ ከላይ የግምቦት ሰባቱን መሪ ገድል በዓለማችን እጅግ ታዋቂ ከሆኑ ነፃ አውጪ ታጋዮች፤ የሃገር መሪዎችና የኖቤል ተሸላሚ ጋር በማነፃፀር፤ ተዓማኒነትና ተቀባይነታቸውን ለማናር ያደረጉት ደረቅ ጥርትዎ ተገምግሟል። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ሊያቀራርቧቸው ካሰቡት ነፃ አውጪ ታጋዮች እጅግ በጣም የሚያራርቃቸው አንድ ወሳኝ ቁምነገር ቢኖር በዓላማቸው ፀንተው በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ለመርጋት የሚያስችል ባህርይና የመንፈስ ፅናት ማጣታቸው ነው። ይህም በድርጅት ውስጥ የሚፈጠሩ ልዩነቶችን አቻችሎ፣ ችግሮችን ቀርፎ ለውጤት ለመብቃት የሚያስችል የመሪነት ብቃትን ጥያቄ ውስጥ ያስገባል። የሃገር ሉዐላዊነትና ዘላቂ የሕዝብ ደህንነትን የሚመለከቱ አሳሳቢ ጉዳዮች እንዲሁ በዘፈቀድ፣ በግርግርና አፈ ጮሌዎች በሚነሰንሱት ከንቱ ውዳሴ ተድበስብሶ ማለፍ የለበትም። ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከሰሜን አፍሪካና ከአንዳንድ የአውሮጳ ሃገራት የቀለም አብዮቶች ያገኘናቸው ተመክሮዎች ቆም ብለን እንድናስተውልና እንድናስብ ያደርጉናል።

2. "ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ" እንደሚባለው የአበው ብሂል፤ ጋዜጠኛ ደምስ በለጠ በሥፍራው ተገኝቶ ያሰባሰበውን፣ የሚያውቃቸውን ግለሰቦችና ክስተቶችን አስመልክቶ ለሕዝብ በይፋ ያቀረበውን መረጃ አጣጥሎ፤ የሻዐቢያን ገመና ለመሸፈን የ"ተናግረው የሚያናግሩ ፎቶዎች!" ፀሐፊ በከንቱ ደክመዋል። ለመረጃ ጥራትና ተዓማኒነት እንኳን አውቃቸዋለሁ ያሉትንና በጽሑፋቸው ላይ ሥማቸው ያልተጠቀሰው "የቁሱ ፎቶ ታሪክዎ" በ "ተናግረው የሚያናግሩ ፎቶዎች!" ላይ ያቀረቡትን አስተያየት ለዛው የተሟጠጠና ጣዕመ ቢስ አድርጎታል።

ከዕምነት ጋር የሚያያዙ ጉዳዮችን ለፖለቲካ ዓላማ ፍጆታ ከማዋል መቆጠቡ ይመረጣል። እራስዎንና ሽንጥዎን ገትረው የሚሟገቱለትን ድርጅትና ግለሰብን ጭምር ግምት ውስጥ ያስገባልና። ማዋሉ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ጥበብና የኲምክና ችሎታን ይጠይቃል። ለዚህም ጊዜ ወስደው የኮሜዲያን ከበበው ገዳ፣ ደረጀና ሃብቴ፣ ልመንህና አለባቸውን፣ መስከረም በቀለ፣ ተስፋዬ ካሳ፣ ተስፋዬ ኢርኪሳ፣ ዳንኤል ቁንጮ፤ የአብረሃም አስመላሽ፤ የፍልፈሉ... አርቲስት ፋንቱ ማንዶዬ፣ አርቲስት ጌጡ አየለን.. ወዘተ ድንቅ ሥራዎችን ማጤኑና ደፍሮም ምክር መጠየቁ ያስከብራል።

ዋቢ ምንጮች፤


1. http://www.ethiomedia.com/102shows/tenagrew_yemianagru_fotoch.pdf
2. http://www.ethiopatriots.org/pdf/awo_ye_ertraw_foto_ynageral150722.pdf
3. ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፡ የዓነት ጎህ ሲቀድ፡ በአሜሪካ፡ ግንቦት 1998 ዓ/ም (እ.አ.አ 2006 ዓ/ም)
4. Prof. Musie Tegegn, Ethiopianizm TV


**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**